# የአምባ ገነኑ መለስ ዜናዊ መሞት ሥር-ነቀል ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ለውጥን በኢትዮጵያችን ያመጣ ይሆን?

ከአቶ ሰውየው ባላገሩ (ከሰሜን አሜሪካ)

ሰሞኑን በስደት ያሉ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የዜና አውታሮች ወሬ መነሻና መድረሻቸው የአምባገነኑ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ሞት አፋፍ ላይ ስለመሆኑ ነው። እንዲያውም በቅርቡ የተመሠረተው የስደት የፖለቲካ ቡድን ማለትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት ወይም በእንግሊዝኛ ስሙ Ethiopian National Transitional Council "..የመረጃ ምንጮች እንደገለጹት.." በማለት ከአራት ቀናት በፊት በፈረንጆች ቀን አቆጣጠር ጁላይ 15 ቀን ባሰራጨው የሚከተለው መግለጫ መሠረት[1] መለስ ሞቷል ብሎናል።

> ከኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ም/ቤት የተሰጠ መግለጫ
> ፈጣሪ የኢትዮጵያን ህዝብ ጸሎት የሰማ ይመስላል
>
> የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ም/ቤት የመረጃ ምንጮች እንደገለጹት አቶ መለስ ዜናዊ በትናንትናዉ እለት ለሊት ቤልጅም ሀገር ህክምና እየወሰደ በሚገኝበት ሆስፒታል ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል። የሽግግር ም/ቤቱም ገዢዉ ስርአት የዚህን ዜና እዉነትነት ለህዝቡ የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት ይላል። የሽግግር ም/ቤቱም መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚሊዮኖች በመዉጣት የተጀመረዉ ትግል ለዘመናት ሲታገልለት የኖረዉን ህዝባዊ መንግስት በመመስረት በድል እንዲጠናቀቅ ትግሉን ሳያሰልስ በቁርጠኝነት እንዲቀጥል በዚህ አጋጣሚ ጥሪዉን ያቀርባል። የሽግግር ም/ቤቱ ዜናዉን በተመለከተ ተከታታይ መረጃዎችን ወደፊት ያቀርባል።
>
> ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ።
> የሽግግር ም/ቤቱ አመራር

በዛሬው ዕለት ይህን መጣጥፍ ስጀምር የምዕራባውያን የዜና ማሰራጫዎች የዲፕሎማሲያዊ ምንጮችን በመጥቀስ መለስ ዜናዊ በጠና ታሞ በአውሮፓ ብራስልስ ከተማ በሚገኝ ሆስፒታል በጣዕረ ሞት ላይ እንደሚገኝ ሲዘግቡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን መንግሥት ወክሎ አቶ በረከት ስምዖን በዛሬው ዕለት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ መለስ ዜናዊ መታመሙን አምኖ በደህና ሁናቴ ላይ እያገገመ እንዳለና የአውሮፓውያንና የተቃዋሚዎች የዜና ማሰራጫዎች ዜናውን ከሚገባው በላይ እያጋነኑ መሆናቸውን አስቀምጦ አልፎአል።

ዛሬ በዚህ መጣጥፍ ለመመልከት የምሻው ስለ አምባገነኑ መሞት ወይም አለመሞት አይደለም ። ለእኔ መለስ ዜናዊና መሰሎቹ የሞቱት የነሡኝነትን ፖለቲካ አንግበው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ጊዜ ገና ከለጋ ወጣትነታቸው ጀምሮ ነው ። እንዲያውም እንደእኔ እምነት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ የጎሣ ፖለቲካን ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ፤ የየትኛውም ጎሣ ወኪል ወይም ነጻ አውጪዎች ብለው ራሳቸውን ቢሰየሙም ፤ ሞተው መቀበራቸውን የማያውቁ የበሰበሱ አስከሬኖች ብቻ ናቸው ።

[1] የአማርኛ መግለጫውን ለማንበብ http://etntc.org/ENTC/wp/wp-content/uploads/Press_release_July04_Amharic.pdf

ትግላቸውም ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት ሳይሆን በሀገራችን ላይ የሚመጡ የሞት ጥላና የሞት መዓቶች ናቸው ። ይህንን የምልበት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተራማጅ ልጆቹ መሪነት ባለፈው 30 እና 40 ዓመታት የጎሳ ፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን የዴሞክራሲ ጥያቄ ተቀጽላ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ወደ ብርሃኑ ወደ ዴሞክራሲያዊነቱ ጎዳና እንዲመጡ የሰጧቸውን መልካም አስተያየትና ዕምነት ቀረጣጥፈው በልተው ዕውነተኛ መልካቸውን (ፋሺሽታዊነታቸውን፣ ከሃዲነታቸውንና ጸረ ኢትዮጵያዊነታቸውን በተጓዟቸው የጭለማ ገድሎች) እጅግ ጸያፍ የሆነና ለሰው ልጅ ጆሮ የሚዘገንን ፣ የእድገትና የአንድነት ፀር የሆነው የአጭር ጊዜ የጥፋት ዘመቻ ታሪካቸው ፣ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ፣ የውድመት መላክተኛ ለመሆናቸው ከበቂ በላይ የሆነ ከፍተኛ ግንዛቤንና ተመክሮን ያካበትኩ ስለሆነ ነው ።

እንዲያውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሃያ ዓመት በሙሉ ሊያስተምሩት የሞከሩት የጎሳና የጥላቻ ፖለቲካ ሥር አልሰድ ብሎ ኢትዮጵያዊነት ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተጠናክሮ በአቸናፊነት ለመውጣቱ የተለያዩ ምልክቶችን ያየንበት ወቅት ነው ። አዲሱም ትውልድ ቢሆን የፈለግነውን እንበለው ፣ አባቶቻችን ያስረከቡንን የኢትዮጵያዊነት ዕምነቱንና ማተቡን አጠንክሮ ይዞ ኢትዮጵያ ወይም ሞት ! ሞት ለከፋፋዮችና ለዘረኞች! እያለ ይገኛል ። ትልቁ ችግራችን መሪ አልወጣልን ማለቱ ብቻ ነው ። ይህም ደግሞ ጊዜ እንደሚያስተካክለው አልጠራጠርም ፤ ይህ ሊሆን እንደሚችልም ፣ ዛሬ ከላይ ታች የሚሯሯጡት ዘረኛ ፣ ጥቅም አሳዳጆች ፣ ገንጣይና አፍራሾችም ጠንቅቀው የሚያውቁት ሃቅ ነው ።

ወደ ተነሳሁበት ርዕስ ከመመለሴ በፊት የአምባ ገነኑ መለስ በድንገት መሞት ጥቅሙና ሊያስከትል የሚችለው አሳሳቢ ሁናቴና መፍትሄውን እንመልከት ።

ከሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተከሰቱት የአምባገነኖች ታሪክ የምንማረው ፣ አምባ ገነኖች ለዘለዓለም ይኖሩ ይመስል ከነሱ ህልፈት በኋላ የሥልጣን ሽግግር የሚኖርበትን ሁናቴ አያመቻቹም ። አምባ ገነኖች እንኳንስ የሚገዙትን ሕዝብ ሊያምኑ ይቅርና በዙሪያቸው የኮለኩሏቸውንም ግዑዝ መሰል ፍጡሮች በስጋትና በአይነ ቁራኛ እየተመለከቱ ሲደነግጡና ሲደነብሩ እድሜያቸውን ሁሉ እንደበረገጉ የሚያልፉ አሳዛኝ ፍጡሮች ናቸው ። በዙሪያቸው የሚኮለኩሏቸውም ሎሌዎች የሚመለመሉት (በብቃትና ችሎታ ሳይሆን፣ በአምቻ ጋብቻ፣ በሆዳምነታቸው ፣ በፈሪነታቸው ወዘተ.. ) በመሆኑ ፣ እነ ሲጠሯቸው አቤት ፤ ሲልኳቸው ወዴት ፤ አሻንጉሊት ባለሥልጣናትንም ስለማያምኗቸው ፣ እርስ በርሳቸው የሚጠባበቁበትን ፤ የሚሰባበቁበትን ሴራ ሲጎነጉኑና የጠለፋ ድር ሲያደሩ የሚውሉ ናቸው ።

መለስ ዜናዊም ላለፉት ሃያ ዓመታት በራሳቸው በወያኔዎች መካከል ሳይቀር ሲመስለው የሚያቀርባቸው ፣ ሲጠራጠር የሚያሸሻቸው ፣ ሲያሻው ደግሞ የሚያገለባብጣቸው ዕቃዎች ፣ እርስ በርሳቸው ከንፈር እየተናከሱ የተቀመጡ ቀን የሚጠብቁ ያደቡ ተኩላዎች ናቸው ። ስለሆነም የወያኔ ሥርዓት በስብሶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተናክሶ ባለበት ባሁኑ ወቅት ፤ መለስ ዜናዊ ከላይ በጠቀስኩት መንገድ የሸረበው የሥልጣን ተዋረድ ብቃት ኖሮት የሚፈጠረውን ክፍተት (Power vacume) ሸፍኖ ሥርዓቱን ለማስቀጠል የሚያስችል አቅምና ችሎታ ይኖረዋል የሚል ግምት የለኝም ። የወያኔም ሥርዓት እንደመለስ ዜናዊ በጣዕረ ሞት አልጋ ላይ ተንጋሎ ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ እያለ መሆኑን እየተመለከትን በደጋፊዎቹና በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ሁሉም ነገር አማን ነው ብለው በባዶ መደሰኩሩ የሚጠበቅ ነው ። ሰውየው ነገ ጧት እንኳ ቢሞትና የሥልጣን ክፍተት ቢፈጠር ፤ ወይም ሕዝቡ ቢነሳሳ ፤ ሕዝባዊው ማዕበል ጠራርጎ ሥር-ነቀል ለውጥ በማድረግ እንዳይጥላቸው የተቻላቸውን ለማድረግ ያለፈውን ሃያ

ዓመታት ችግር ሁሉ በመለስ ላይ ደፍድፈው ሥርዓቱን በልዩ መልክ ነፍስ ሊዘሩለት የሚሞክሩ ሀገር በቀልም ሆኑ የውጭ ኃይሎች ብቅ ማለታቸው አይቀሬ ነው ።

ከሁሉም በላይ ጸረ ኢትዮጵያና ፣ ጸረ ዴሚክራሲያዊ አጀንዳ ይዘው ስለ ኢትዮጵያዊነትና ዴሞክራሲያዊነት የአዞ እንባ እየረጩ ፣ ሲቻላቸው የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ በራሳቸው ለመተካት ፣ እንደ አማራጭ ኃይል ሆኖ መቅረብ ፣ ባይቻላቸው ደግሞ ፣ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኘውን ሥርዓት በድርድር ሰበብ ገብተው በሥልጣን ዕርከን ላይ ቁጢጥ ለማለት  የሚፈልጉ ሁሉ በዚህች ጊዜ እንደሚሯሯጡ ለአንድ አፍታ መዘንጋት የለበትም ። ድርድርን አስመልክቶ ሰሞኑን በተለያዩ የፓልቶክ ውይይት መድረኮች ከመለስ በኋላ ስለመደራደር  ውይይቱ በሠፊው ተጧጡፏል ። ለመሆኑ ኢትዮጵያዊው ኃይል በዕቅድ ተበታትኖ ባለበት ሁናቴ ማን ነው ከማን ጋር የሚደራደረው ብለን ጠይቀናል?  ለድርድርም እኮ የኃይል ሚዛን አስፈላጊ ነው ። በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገራችን እንዲሰፍን የሚሻው አመዛኙ ኃይል በውስጡ መተማመንን የሚገነባበትን ሁናቴ ባስቸኳይ መፍጠር አለበት ። በተለይም ይህ መተማመን እንዳይመጣ በመካከላችን ሌት ተቀን ልዮነቶቻችንን የሚያሰፉና የሚያራግቡትን ለይቶ በማውጣት ፣  ዳግም የሃገራችን ሁኔታ በገንጣዮችና በዘረኞች እጅ እንዳትወድቅ ከምን ጊዜውም በላይ በትጋት መሥራት ይኖርብናል ። ኢትዮጵያዊነትን በማጉላት የሀገር አንድነትንና የዲሞክራሲን አስፈላጊነት ባልተንሸዋረረ መልኩ አቅጣጫ በማስያዝ ብዙሃኑን አሰባስበን ጠንካራ ኃይል ሆነን ለመውጣት እንዲቻል ጥረቱ ባጭር ጊዜ ሊጧጧፍ ይገባል ።

ለማጠቃለል፦

በርዕሱ ያነሳሁት ጥያቄ ያምባገነኑ መለስ ዜናዊ መሞት ሥር-ነቀል ዴሚክራሲያዊ ሽግግርን ሊያመጣ ይቻላል ወይ ለሚለው ፤ መልሱ፤- ወያኔ በተዘረፈጠበት ሃያ ዓመታት ውስጥ በያንዳንዷ ቀን ውስጥ ይቻል ነበር ። ችግራችን የመሪ ማጣት ጉዳይ ነው ። እስኪ ከመጀመሪያ አንስተን ራሳችንን እንመርምር ። ወያኔዎች ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ  በሀገር ላይ ሊያመጡ የሚችሉትን ጥፋትና ውድመት ገሃድ አድርገው ያሳወቁንንና ወያኔን ሲታገሉ የነበሩትን ገፍትረው ጥለው ፣ ልጆቻችን ናቸው ፤ ብለው እንድናቅፋቸው ያደረጉንን መሪ ተብዬዎች  ያደረሱትን የአመራር ግድፈት ለአንድ አፍታ ዞር ብለን ስናስታውስ ብቻ ነው ታሪክ እራሱን እንዳይደግምና ለወደፊቷ ኢትዮጵያችን ሥር-ነቀል ለውጥ ለማምጣት ምን ማድረግ እንደሚያስፈልገን የምንገነዘበው ። ዛሬም የጎሣ ፖለቲካ አራማጆችን ጥያቄ መልስ ልንሰጠው ይገባል በሚል ባዶ ወሬ፣ ኢትዮጵያ በሬፈራንደም እንደገና እንደ አዲስ ሀገር መመሥረት አለባት፣ ዴሞክራሲያዊነት የሚጠይቀው ይሄንን ነው የሚሉን ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መድረኩን አጣበውት ለሌላ ዙር የጎሣ ፖለቲከኞች ጥፋት እያዘጋጁን ለመሆኑ በግልጽ የሚያደርጉት ቅስቀሳ ያመላክተናል ። ኢትዮጵያ የጎደላት ተሟልቶና ተስተካክሎ ፣ የወያኔው የበታኝና ያፍራሽ ስርአት ከመቃብር ተጥሎ ባዲስ ህዝባዊና ፣ ዲሞክራሲያዊ መልክ ተዋቅሮና በመከባበር ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ወደፊት መቀጠል ይኖርባታል እንጂ ኢትዮጵያችን ፈራርሳ እንደገና ትገንባ የሚለው የበታኞችን አካሄድ አጥብቀን ልንዋጋው ይገባናል ።

በኢትዮጵያዊነታቸው ከፍተኛ ዕምነት ያላቸውና በሀገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በወያኔና መሰሎቹ ጎሠኝነት መቃብር ላይ ማበብ አለበት ብለው የሚያምኑ የፖለቲካ ስብስቦች ፣ በግለሰብም ሆነ በድርጅት "አይሆንንም ትተሸ ይሆናልንም በጨመርሽ" እንዲሉ የመለስ ዜናዊ መሞት በሥርዓቱ የመንገዳገድ ሁናቴን ሊፈጥር ይችላል ብለው በማሰብ ፣ ይህንን ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሊከፈት

የሚችለውን የሥልጣን ክፍተት ቀዳዳ በማስፋት ወያኔዎች ሊቆጣጠሩት ከማይችሉት ቀውስ ውስጥ ለማስገባት ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመጠየቅ የሥር ነቀሉን ፍልሚያ ለመለኮስ በተጠንቀቅ ላይ በድርጅትም ሆነ በማንኛውም ረገድ ዝግጅታቸውን ማጠናቀቁ የትላንትና የቤት ሥራቸው መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም ። ከሁሉም በላይ ወያኔም ሆነ ጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ይህ ሁናቴ ሊፈጥር የሚችለውን ግርግር ወደ ጎሣ ወይም የኃይማኖት መተላለቅ እንዲያመራ ሊገፋፉ ስለሚችሉ ፤ ወገኖች በማንኛውም ምክንያት እርስ በእርስ እንዳይጨፋጨፉ የመሪዎችም ሆነ እንዲሁም ለሃገርና ለወገን ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ኢትዮጵያዊ ዜጎች ሁሉ በአስተዋይነት ፣ በብልህነት ፣ መጓዝ እንደሚገባቸው አስቀድመው መረዳት ያለባቸው እንደሆነ ማወቁ ተገቢ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥር-ነቀል ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በምንም መልኩ

- ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አይጣፍጥም እንዲሉ ያለውን ሥርዓት ወሻሽሎ ማስቀጠል እንዳልሆነ፤ ወይም የጎሳን ፖለቲካ በጓሮ በር ማስገባት እንዳልሆነ ማጤንን ይጠይቃል
- ኢትዮጵያን በሬፌራንደም እንደገና ቆርጦ መቀጠል እንዳልሆነ መገንዘብን
- የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስንል አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚዊክል ሥርዓት መመሥረትና ሀገሪቱ የምትተዳደረው በየእርከኑ የሚያስተዳድሩን የአብዛኛውን ሃሳብ የጊዜው መተዳደሪ ፖሊሲያችን እንዲሆን በጋራ የምንስማማበት ቢሆንም ውሁዳን (ማይኖሪቲ) የሚያንሸራሽሩት ሀሰብ ነገ የአብዛኛው እንዲሆን የሚያደርጉት የተቃውሞ እንቅስቃሴ መገታት አለበት እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። ከሁሉም በላይ ሊሰመርበት የሚገባው ስለዴሞክራሲ ስናወራ የግለሰብ ነጻነት የመጀመሪያው የውሁዶች (ማይኖሪቲ) መብት መሠረት እንደሆነ ሊረጋገጥ ይገባዋል።

በመጨረሻም ሥር-ነቀል ዴሞድራሲያዊ ለውጥን የሚያራምዱ ቆራጥና ተጠያቂነትን የሚያውቁ የትግል መሪዎቻችን ሊሆኑ የሚችሉትን በጥንቃቄ መምረጥና ከፊት ማስቀደም ያስፈልገናል። ግርግር ለሌባ ያመቸዋል ነውና በዚህ ጊዜ የተላያዩ ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ሃሳዊ መሪዎች ሽምቅ አጀንዳቸውንና ተልዕኮአቸውን አንግበው መሪነቱን ለመቀማት ከየሥርቻው ብቅ ማለታቸው አይቀሬ ነው፣ ያለፉት ሃያ ዓመታትም የውሸት መሪዎች በየሳምንቱ መፈልፈል ብዙ አስተምሮናል፤ ዛሬም እንዲሁ። እኛም እነ ማናችሁ? የት ነበራችሁ? ብለን አገለባብጠን ማንነታቸውን መመርመርና ዕውነተኛውን መሪ ከውሸታሙ መለየት ግዴታችን ነው። መሪዎቻችንን እንደጽላት ተሸክመን እግዚኦ ይምንል ሳይሆን ጠራርበን ልንቀርጻቸው እነሱም ሊያውቁት እኛም ተከታዮቻቸው ዋናው ተግባራችን መሆኑ በግልጽ ልንተዋወቅ ይገባል። ከዚህ በኋላ የምንፈልጋቸው መሪዎች ትግሉን የሚያፍፍሙ እንጂ በተለያየ ምክንያት እያግቸለቸሉ ሽብረክ የሚሉና ትግሉን የሚያስሙቱ መሪዎችን አንሻም።

ላንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያችን ትውልዶች የተዋደቁለትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት ሁላችንም በያቅጣጫው የያቅማችንን መግፋት እንዳለብን በጥሞና መገንዘብ ያሻናል።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል

የከርሞ ሰው ይበለን

አቶሰውየው ባላገሩ (ከሰሜን አሜሪካ) (July 20, 2012)